# ቅዱሳንና ክብራቸው

«ዛሬ በፈቃዱ ራሱን ለእግዚአብሔር የሚቀድስ ማነው?» ቀዳማዊ ዜና መዋ.ምዕ. 29 ፡5

ከዚህ መልዕክት እንደምንረዳው እግዚአብሔርን ለማገልገል ራስን መለየት እንደሚገባ ነው። ከቃሉ ትርጉም ስንነሳ «ቀደሰ» የሚለው ሐረግ የሚያመለክተው «ለየ» «አከበረ» መረጠ ሲሆን ስን ተረጉመው «ዛሬ በፈቃዱ ራሱን ለእግዚአብሔር የሚለይ ማን ነው?» የሚለውን ይሆናል።

በዚህ የትምህርት ክፍል የምንመከተው ስለ ቅዱሳን ክብርና ጸጋ ሲሆን በህይወት ሥጋ/ስለላቸው መንፈሳዊ አገልግሎትና ዘለዓለማዊ ክብር እንመልከት።

**ቅዱሳን ማለት ምን ማለት ነው?**

ቅዱሳን ማለት እግዚአብሔርን ለማገልገል ከወገኖቻቸው የተለዩ

- ከሥጋዊ ኑሮ መንፈሳዊውን የመረጡ
- ከህግ በላይ በመሆን ህግን ፈፅመው ብሎም በራሳቸው የተቀደሰን ህግን በሥራ ተርጉመው የሚኖሩ
- በራሳቸው የተቀደሰን ህግ በሥራ ተርጉመው የሚኖሩ
- ዓለምን ርቀው ንፅህናቸውን ጠብቀው ያሉ
- ከራሳቸው ክብር ይልቅ ለእግዚአብሔር ክብር የሚቀኑ
- የአምላካቸውን የመስቀል ውልታ አስበው የሚያለቅሱ
- የወገኖቻቸው ኃጢአት የሚያስጨንቃቸውና ስለ ወንድሞቻቸው መዳንን /ድህነትን / መውረስ ዘወትር የሚፀልዩ ባጠቃላይ «ከሕጋ-ሥጋ ሕገ-ነፍስ ሕገ-እንስሳ ሕገ-መላዕክት» ይበልጣል ብለው ፈጣሪያቸውን በሕይወት ዘመናቸው ሳያስቀድሙ በምስጋና በጸሎት ተወስነው የሚኖሩ ቅዱሳን ተብለው ይጠራሉ።
- እውነትም ራስን ለእግዚአብሔር ከመለየት ጠዋትና ማታ ያለዕረፍት እንደቅዱሳን መላዕክት ማገልገልን የመሰለ ጸጋ ምን አለ?

  አዎ! ቅዱሳን እንደመላዕክት ለመሆን ህገ-መላዕክትን መርጠዋል ብለናል ለመላዕክት የተሰራላቸው የተቀረጸላቸው ምን ሕግ አላቸውና ብለው ቢጠይቁን መልስ ለመስጠት እንድን ችል ቀጣዩን መልዕክት እንመልከት።

  ሕገ-እንስሳና ሕገ-መላዕክት ምንድን ናቸው? ሕገ-እንስሳ የምንለው ስንመለከት ለእን ስሳት ሕግ መተዳደሪያ መመሪያ ኖሯቸው ሳይሆን ባህሪያቸውን ለመግለፅ ነው።

  በመሆኑም እንስሳት በባህርያቸው

- መብላት መጠጣት
- መውለድ መዋለድ
- በደመ ነፍስ መኖርና ሞቶ በስብሶ መቅረት

ስለሆነ መብላት መጠጣቱን መውለድ መዋልዱን ጥለው ራሳቸውን ለተቀደሰው አገልግሎት መላዕክትን በመምሰል ይኖራሉ ለማለት ነው።

- አይበሉም አይጠጡም
- አያገቡም አይጋቡም
- አይወልዱም አይዋለዱም
- አይሞቱም አይፈርሱምና

«ምስጋቸው ምግብ ምግባቸው ምስጋና» ሆኖአቸው በክርብና ይኖራሉ እንጅ «ወምግቦሙ አኮቴቶሙ ምግቦሙ» እንዲል።

መላዕክት ፥ ሕያዋን ፍጥረታት ናቸው

- ለምስጋና ለቅዳሴ ለዝማሬ አይደክሙም
- ያለእረፍት ያለመሰልቸት እግዚአብሔር አምላካቸውን ያመሰግናሉ።

ስለዚህም ነው ከህገ-ሥጋ ህገ-ነፍስ ከሕገ-እንሰሳ ህገ-መላዕክትን መርጠው ማገልገል የፈቀዱት። ቅዱሳንም ባህርየ እንስሳን ጥለው ባህርየ መላዕክትን መምረጣቸው

1ኛ. አምላካቸውን ደስ ለማሰኘት

2ኛ. ዘለዓለማዊ ክብርን ለማገኘት

3ኛ. ለወገኖቻቸው ለመጸለይና ድህነትን ምህረትን ለማሰጠት ነው።

ቅዱሳንም ፈጣሪያቸውን ከማገልገል በላይ ሌላ ታላቅ ነገር እንደሌለ በመገንዘባቸው ያገለገሉት አምላክ ጽድቅን አድሏቸው ጻድቃን ተብለዋል።

<u>ፃድቃን ማለት ምን ማለት ነው?</u>

<u>ፃድቅ</u> ማለት ከቃሉ ቀጥተኛ ትርጉም እንደምንረዳው የጸደቀ ኩነኒ በደል ያላገኘው የገሃነም እሳት ፍርድ ያልተፈረደበት እንደሆነ እናምናለን። እንደ ቅዱሳት መጻሕፋት አባባል ዳግመኛም ስን መለከት ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት እንዲህ አለ።

«አፉሁ ለፃድቅ ይትሜሐር ጥበበ ወልሳኑ ይነብብ ፅድቀ ወሕገ አምላኩ ዉስተ ልቡ ይላል።»

ነቢየ እግዚአብሔር እንደገለጸው ፃድቃን ለህግ ሰዎች እንደሆኑ እንረዳለን። በዝርዝር ለመመልከት እንሞክር።

ሀ/ አፉሁ ለፃድቅ ይትሜሃር ጥበብ ማለት ፥

የፃድቅ ሰው አፍ /አንደበት/ ጥበብን ትናገራለች/ታወራለች/ ማለት ሲሆን በሌላ አነጋገር ፃድቅ ማለት እውነተኛ ስለ እውነት የሚናገር ማለት ነው።

ጥበብ የሚለው ደግሞ «እግዚአብሔር» ማለት ነው። የአምላክ ስም ነውና ማለትም ስለ እግዚአብሔር ክብር ታወራለች። ስለ እግዚአብሔር የእጁ ሥራ ስለጥበብኛው አምላክ ታውራለች ማለት ሲሆን «ጥበብሰ መድኃኒነ ውዕቱ ወቢዘወነ በጥብሃ ሥጋሁ ወተሳየጠነ በንዝሃተ ደሙ ወሃሪነ ለመንግስቱ » እንዲል።

ጥበብ የተባለው መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲሆን ትርጉሙ «በሥጋው መቆረስ የተቢዥን በደሙ መፍሰስ የታረቀን የቀደሰን» በመንግስቱ /ለመንግስተ ሰማያት/ የመረጠን ማለት ነው። ይህን ን የአምላክ ውለታ ቅዱሳን አውቀው ተናግረውታልና እንዲህ አለ።

ለ/ ወልሳኑ ይነበብ ፅድቀ ፥

- አንደበቱም ፅድቅን ይናገራል
- አንደበቱም ፅድቅ እውነትን ይመሰክራል።

ሐ/ ወሕገ አምላኩ ውስተ ልቡ ፥

የአምላኩ የእግዚአብሔር ህግ በልቦናው ሁሌ ተቀርጿልና የአምላኩ ህግጋት በልቦናው ተቀርጾዋልና የሚሰራውን ሥራ ሁሉ በልቡ ያለው ህግ እግዚአብሔር ይመራዋልና ማለት ነው። ጠቅለል ባለ መልኩ ቅዱሳን /ፃድቃን/ ፥

- የጥበብ ሰዎች /የእግዚአብሔር ምርጦች/
- የፅድቅ ወራሾች /የክብር አምላክ ባለሟሎች/
- ሕግ አክባሪና አስከባሪ የሕግ ሰዎች ናቸው።

<u>የቅዱሳን ክብር በአጸደ ሥጋ</u>

ቅዱሳን የእግዚአብሔር ወዳጆች ስለመሆናቸው ለቅድስናም የበቁት ከራሳቸው ፈቃድ ይልቅ የእግዚአብሔር የአምላካቸውን ፈቃድ አስቀድመው በመኖራቸው በእግዚአብሔር ፈቃድ ለቅድስና በቅተዋል በህይወተ ሥጋ ሳሉም ሆነ ከአረፍት /ከሞት/ በኋላ እግዚአብሔርን የሚያመልኩ በህጉ የሚኖሩና ኖረው የነበሩ አይሞቱም ካልን በቅድሚያ በህይወተ ሥጋ ሳሉ ክብራቸውን በመጠኑ እን መልከት።

1ኛ. አብርሃም የሚወደው ልጁን ለመስዋዕት ያቀረበ

አብርሃም ፥ አብርሃም ህግ ሳይኖር ፈጣሪውን በህገ ልቦና ያከበረ ሰው ነው።

- አባታችን አብርሃም አምላኩን ፈልጎ ያለጥርጥር ያለመከ ሰው ነው።
- የአምላኩን ድምፅ ሰምቶ ከሃገር ከወገን ከዘመድ የተለየ ነው።

- አምላኩ እግዚአብሔር ዘሩን እንዲባርክለት የለመነና የቃል ኪዳን ባለቤት ታላቅ አባት ነው።
- ከፈጠሪው ዘንድ የባረኩህን አባርካለሁ የረገሙህን እረግማለሁ ዘርህን እን ደሰማይ ከዋክብት እንደምድር አሸዋ አበዛዋለሁ የተባለለት ታላቅ የእግዚአብሔር ባለሟል ነው።
- የዓለምን ከንቱነት አውቆና ተረድቶ በመንገድ ደር ድንኳን ተክሎ ይኖር የነበረና በተለይ ከትዕዛዝት አንዱን በአደባባይ በሥራው ያስመሰከረ እን ግዳ ተቀባይ ታላቅ አባት ነው።
- በእንግዳ ተቀባይነት ስላሴ ዓለምን የፈጠሩ «ሥሉስ ቅዱስ» በቤቱ ገብተው ማዕዱን የባረኩለት ቡርክ ሰው ነው።

በዚህ ዓይነት ህይወቱን አባታችን አብርሃም ያላሰበውና ያልጠበቀው ፈተና ገጠመው ። በእን ግድነተት ሳለ በጌራራው ንጉሥ በአቤሜሌክ በሚስቱ በክብርት ሳራ ተፈተነ አቤሜሌክም ሳራን ለፍትወት ተመኝቶ ወደ ቤተ መንግስቱ ቢያስገባትም አብርሃምን ለክብር የጠራ አምላክ ሥጋው እን ዲረክስ አይፈልግምና የደፋሩን የአቤሜሌክን ሰውነት በእባጭ ቀጥቶ በህልምም የአብርሃምን ክብር ገልፆ እንዲጸልይለት እርሱ ካልጸለየለት እንደማይድን ነግሮ ያከበረው ታላቅ የልዑል እግዚአብሔር ባለሟል ነው።

ነቢይ ነውና ስለ አንተ ይጸልያል ትድናለህም አብርሃምም ለአቤሜሌክ ለህዝቡ ጸለየ ሁሉም ተፈወሱ።

ከዚህ ዓረፍተ ነገር የምንማረው ከንጉሡ ከአቤሜሌክ ይልቅ ነቢዩን አብርሃምን እንደመረጠውና እንዳከበረው ክብሩንም ለንጉሡ እንደገለጸለት ነው።

እንዲሁም እግዚአብሔር የመረጠው አባት በመሆኑም ከኃጢአት የረከሱና ፈጣሪያቸውን ያሳዘኑ የሰዶምና የገሞራ ሰዎችን ቅጣት ባሰበ ጊዜ እግዚአብሔር አምላክ ወዳጁ አብርሃምን አክብሮ ክብሩን በገሃድ ገልፆ እንዲህ አለ «በውኑ እኔ የማደርገውን ከአብርሃም እሰውረዋለሁ» አብርሃም በእውነት ፃድቅና ብርቱ ሕዝብ ነው። አለ አብርሃምም የእግዚአብሔር ባለሟል እንደሆነ ከተረዳ በኋላ ስለ ሰዶምና ገሞራ ህዝቦች ምልጃን እንደጀመረና ፈጣሪውን እንደለመነ እንረዳለን።

2ኛ. ሙሴ ከእግዚአብሔር ህዝቦች ጋር መከራን ተቀበለ

- ከእግዚአብሔር ህዝብ ከቤተ እስራኤል የተወለደ
- በባህር ተጥሎ የተገኘና የእግዚአብሔር ተዓምር የተገለጠለት
- በፈርኦን ቤት አድጎ የፈርኦን የልጅ ልጅ መባልን ያልፈለገ

- ከግዞተኞች ዕብራውያን ጋር የተቀላቀለ
- ታቦተ ህግን በደብረ ሲና ከአምላኩ በክብር የተቀበለ
- ይህ ታላቅ የእስራኤል ነቢይና መሪ የልዑል እግዚአብሔር ባለሟል በፀሎቱ በምልጃው ፈጣሪውን እና ህዝቡን እንዴት ያስተርቅ እንደነበር እን መለከት

ሀ. የእግዚአብሔር ትዕዛዝ አልሰማ ያለው የግብፁ ንጉሥ ፈርኦን ሃገሩን እንቁራሪትና ጓጉቸር ፣ ተናዳፊ ዝንብ በወረረበት ጊዜ ይህንን ታላቅ መቅሰፍት ተመልክቶ ሙሴንና አሮንን አስጠርቶ እንዲህ አላቸው « ይህ መቅሰፍት ጓጉንቸርና እንቁራሪት ከእኔና ከህዝቤ እንዲርቅ ፀልዩልኝ» በማለት ለመነ ሙሴም በእግዘአብሔር ፊት በክብር ቆመ መለመን መፀለይ መማለድ ጀመረ እግዚአብሔርም የወዳጁን የሙሴን ልመና ተቀብሎ መቅሰፍቱን ከግብፃውያን አስወገደ ስለ ወደጁ ስለ ሙሴ ልመና ብሎ።

ለ. እስራኤላውያን አምልኮተ እግዚአብሔርን ጥለው ጣኦትን አምልከው ፈጣሪያቸው በተቀየማቸው ጊዜ የሙሴን ምልጃ በመፈለጉና ክብሩን ሊገልፅለት ወደ« ይህንን ህዝብ አጠፋዋለሁ አንተንም በታላቅ ህዝብ እሾምሃለሁ» ቢለው ጻድቁ አባት ሙሴም እግዚአብሔርን «አቤቱ አምላኬ ሆይ ከጥፋትህ ተመለስ ለአብርሃም ለይስሐቅ ለያዕቆብ የገባኸውን ኪዳን አስበህ ህዝብህን ይቅር በል ካልሆነ ግን እኔን ባርያህን ከጻፍከኝ ከህይወት መጽሐፍ ስሜን ደምስስ አለ።» ግሩም ድንቅ ልመና! ማነው እሱ?

ለ.1. የአባቶችን ቃል ኪዳን አስቦ ፈጣሪውን ስለ ህዝቡ የሚለምን?

ለ.2. ስለ ወገኑ ብሎ እኔንም ደምስሰኝ አለዚያ ስለ እኔ ስትል ለህዝብህ ምህረትን ላክ የሚል? የእግዚአብሔር ቅዱሰን አይደሉምን?

ሐ. እግዚአብሔርም በደመና ዓምድ ወረደ በድንኳንም ደጃፍ ቆመ አሮንና ማርያምን በቁጣ ቃል ተናገራቸው እንዲህም አለ «በመካከላችሁ ነቢይ ቢኖር እኔ እግዚአበሔር በራዕይ እገለጣለሁ በራዕይም እናግራዋለሁ ባሪያዬ ሙሴ ግን እንዲህ አይደለም እርሱ በቤቴ የታመነ ነው። አፍ ለአፍ ወይመ ቃል ለቃል በግልጽ አገነጋግረዋለሁ በምሳሌም አይደለም የእግዚአብሔርን ም መልክ ያያል» በማለት የኢትዮጵያዊቷን ቆንጆ ብላቴናና የሙሴን ጋብቻ በመንቀፋቸው ማርያም ለምፃም ሆነች ኋላም ሙሴ በጸሎት ፈውስን ሰጥቷት እግዚአብሔርን አከበረች።

3ኛ. ኤልያስ ሰማይን የለጎመ

ኤልያስ ከእስራኤል የተመረጠ የእግዚአብሔር መልክዕተኛ

- በበረሃ የሚኖር በዋሻ የተከተተ የእግዚአብሔር ሰው

- የአምላኩ የእግዚአብሔር ቃል አዋጅ ተናገረ
- በረሃቡ ዘመን የድሃዋን መበለት ቤት በተባረከው ጸሎት ለእርሷና ለልጇ ቤቷን በበረከት የሞላአ
- ልጇ የሞተባትን መበለት ሀዘን ተመልክቶ በጸሎትና በምልጃ ከሞት ያስነሳላት
- ኃጢአተኛና አረማዊ የሆነውን ህዝብ በረሃብ የቀጣ
- 3 ዓመት ከመንፈቅ ሰማይንና ምድርን በቃሉ የዘጋ
- በመጨረሻ ቀን ምስክር እንዲሆነ በአውሬው ፊት እንዲመሰክር በህይወቱ ሳለ የተሰወረ (በክብር ቦታ ያለ)
- በእሳት ሰረገላ ተቀምጦ በመላዕክት ታጅቦ ወደ ሰማይ የወጣ
- የለበሳት የልብሱ ዘርፍ ተዓምር የሰራችና ባህር የከፈተች ታላቅ የእግዚአብሔር ሰው ኤልያስ ነቢይ ነው

ከዚህ የምንረዳው ቅዱሳን የገቡበት ቤት በበረከት እንደሚሞላ ትንፋሻቸው በረከሰ መብልና መጠጥ ባለመርከሱ መንፈስ ቅዱስ አድሮባቸዋልና። መድኃኒት ሆነው ሙታንን የሚያነሱ እግዚአብሔርም ከብዙ ህዝብ ይልቅ የተመረጡ ወዳጆቹን ቃል እንሚሰማና ለኤልያስ የሰጠው ሙብት እንኳን ሰማይን ምድርን እስከ መለጎምና ማዘዝ እንደደረሰ ስንመለከት ማነው ዛሬ በዓለማችን ያለ ታላቅ ሰው ሰማይንና ምድርን የሚያዝዝ

4ኛ. ኤልሳዕ የቀርሜለስ ባህታዊ

- በቀርሜሎስ ተራራ በጸሎት ተወስኖ የሚኖር
- የአባቱ የኤልያስ መንፈስ በእርሱ ያደረ
- የድሃዋ መበለት ልጅ ከሞታ ያስነሳ
- የዓለም ኑሮውን ጥሎ ፈጣሪውን ያገለገለ ቅዱስ አባት እና ነቢይ ነው።

5ኛ. ኢዮብ የትህትና አባት (መምህረ ትዕግስት)

- በምስራቅ ካሉ ሰዎች በወቅቱ እጅግ ባለጸጋ የነበረ
- ልጆቹና ሃብቱ በአንድ ላይ ቢጠፉ ፈጣሪውን ያላማረረ
- ሰውነቱ በደዌ ሲመታ እግዚአብሔርን ያመሰገነ ያላማረረ
- ስለ ጓደኞቹ ጥፋት በእግዚአብሔር ፊት ለምልጃ የቆመ

ከዚህ በላይ በጥቂቱ ለመጥቀስ እንደተሞከረው የቅዱሳንን ክብር ለመግለጽ መደርደርያ ይሆናሉ ብለን በማሰብ ሲሆን በቅዱሳት መጻህፍት ስለ ቅዱሳን ምልጃ በስፋትና በጥልቀትበርቀት

የመንመለከተው ከዘመኑ መናፍቃን ስለ ቅዱሳን የሚሰጠውን ስንኩል የሆነ የክህደት አመለካከትእየተመለከትን ከቤተ ክርስቲያኗ ትውፊትና ምስጢራት አንጻር በሰፋት እንመረምራለን።

መናፍቃን ስለ ቅዱሳን ምን ያውቃሉ?

ቤተክርስቲያን ስለ ቅዱሳን ትመሰክር እንጂ « እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ቅዱስ ነኝና እናን ተም ቅዱስ ሁኑ።» ዘሌ. ምዕ.19 ቁ. 2

ቅዱስ እግዚአብሔር ለእስራኤል መምህር ለሾመው ለሊቀ ነቢያት ሙሴ የተናገረው አምላካዊ ቃል ሲሆን የሃዲስ ኪዳን ባለሟልና ሐዋርያ የተባለው ቅዱስ ጴጥሮስም ይህንኑ ቃለ አምላክ መሠረት በማድረግ በቀዳማዊ መልዕክቱ እኔ ቅዱስ ነኝና ቅዱሳን ሁኑ ተብሎ ስለተጻፈ የጠራችሁ ቅዱስ እንደሆነ እናንተም ደግሞ በኑሮአችሁ ሁሉ ቅዱሳን ሁኑ በማለት ይህንን የቅድስና ህይወት መኖር እንደሚገባ አስተምሮናል።